# የኢህዴን-ብአዴን ታሪክ ከ1973 - 2008 መጸሀፍ ይዘት ሲፈተሽ

ሲሳይ መንግስቴ አዲሱ

***መግቢያ***

በዋነኛነት የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲ/ሠራዊት (ኢህአፓ/ሠ) ጠንካራ ወታደራዊ ክንፍ ከነበረው የበለሳው ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ አባላት መካከል በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ አልፈው፣ በትግል ጽናታቸው ተፈትነውና በአመለካከታቸው ጥራት ነጥረው በወጡ 39 አባላት የተመሰረተው የኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኢህዴን) የአሁኑ ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) ታሪክ በትክክልና በተሟላ መልኩ እንዲጻፍ አጥብቀው ይፈልጉ ከነበሩ ሰዎች መካከል አንዱ ስለሆንኩ የኢህዴን-ብአዴንን ታሪክ የያዘ መጽሀፍ በድርጅቱ ከፍተኛ አመራር ውሳኔ መነሻነት በተወሰኑ መስራችና ከፍተኛ አመራሮች አማካኝነት ተዘጋጅቶ በማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት ሀላፊነት መታተሙን ስሰማ በጣም ተደስቼ የነበረ ከመሆኑ የተነሳ መጽሀፉን አግኝቼ ለማንበብ በእጅጉ ጓጉቼ ነበር፡፡

ሆኖም ያ በእጅጉ የጓጓሁለት ‘መጽሀፍ’ በእጄ ገብቶ ገና መግቢያውን ማንበብ ስጀምር የጠበቅሁትን ያህል የተሟላና ታሪክ ነጋሪ ሆኖ ላገኘው ባለመቻሌ በእጅጉ ከመበሳጨቴ የተነሳ ለጊዜውም ቢሆን የማንበብ ፍላጎቴን ተፈታተነው፣ ይህም ሆኖ የታሪኩን ፍሰት በተሟላ መልኩ ለማወቅ ከነበረኝ ብርቱ ፍላጎት የተነሳ ንባቤን በትግልም ቢሆን ቀጥየ በማጠናቀቁ የፈጠረብኝን ስሜት ለመግለጽ ስለፈለግሁ ይህችን አጭር መጣጥፍ ለማዘጋጀት ቻልሁ፡፡

በመሆኑም መጽሀፉ ውስጥ የተስተዋሉ መሰረታዊ ችግሮችን ዝርዝር ቀጥሎ በሚገኙት አንቀጾች ለመመልከት የምንችል ሆኖ መጽሀፉ እውነት ነው የምላችሁ በስርአቱ ታስቦበት የተዘጋጀና ለታሪክ ሰነድነትም እንዲበቃ ተብሎ የተጻፈ ሳይሆን በይድረስ ይድረስ ስሜት ውስጥ ተሁኖ በግብር ይውጣ አይነት አቀራረብ የተጻፈ ይልቁንም አዘጋጆቹ ሀላፊነት የጎደለው ስራ መሰራታቸው በግልጽ የተንጸባረቀበት መሆኑን ለመገንዘብ ግን ጊዜ አልወሰደብኝም፡፡

ይህም ሆኖ ከዚህ ቀደም ከነበረው የተበጣጠሰና ከወሬ ያላለፈ የታሪክ አያያዝና አዘጋገብ ሁኔታ በተለየ አኳኋን የድርጅቱ የትግልና የድል ታሪክ ጠቅለል ባለ መልኩም ቢሆንም እንዲህ በአንድ ሰነድ ተዘጋጅቶና የድርጅቱን ከፍተኛ አመራር ይሁንታ በማግኘት ታትሞ ለተደራሲያን መቅረቡ በራሱ እንደ መልካም ጅምር ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ከዛም አልፎ ይህንን ታሪካዊ ሰነድ መነሻ በማድረግ በህይወት የሚገኙ መስራቾችና በትግሉ ሒደት ውስጥ ክቡር መስወአትነት የከፈሉ ታጋዮች በስርአቱ የሚታወሱበት እንዲሁም ከምስረታው ጀምሮ በከፍተኛ አመራርነት እየተመረጡ ድርጅቱን በመምራት አሁን ላለበት ደረጃ እንዲደርስ የራሳቸውን አስተዋጽኦ ያበረከቱ ታጋዮች ግለ-ታሪክ በራሳቸው ተነሳሽነት አሊያም በሞያተኛ ታግዘው ሊጻፍ የሚችልበትን አማራጭ ተግባራዊ ማድረግ ለነገ የሚባል ጉዳይ አይሆንምና ከወዲሁ ሊታሰብበት እንደሚገባ በዚህ አጋጣሚ ማስገንዘቡ ጥሩ ነው፡፡

በሌላ አነጋገር ድርጅቱም ሆነ ይህን ሰነድ በማዘጋጀት ረገድ ግንባር ቀደም ሚና የተጫወቱ መስራቾች የሚጠበቅባቸውን ያህል ሰርተዋል ባይባልም ችሎታቸውና ስሜታቸው የፈቀደውን ያህል ተንቀሳቅሰው ይህንን ሰነድ አዘጋጅተው በማቅረባቸው በራሱ ሊመሰገኑ ይገባል እላለሁ፡፡

ይሁን እንጂ ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርሁት ይህንን ያልተሟላና የድርጅቱን ታሪክ በትክክል ያላንጸባረቀ ሰነድ በትዕግስት አንብቤ እንደጨረስሁ በጊዜው የተፈጠረብኝን ቁጭት እንዲሁ በዝምታ ከማልፈው ይልቅ በጽሁፍ መልክ አስፍሬ ሌሎች ያገባናል የሚሉ ወገኖችም ሀሳቤን እንዲጋሩት ማድረግ እንዳለብኝ በማመን የተመጠነ ምልከታየን በሚከተለው አኳኋን አቅርቤዋለሁና አንዳች ትምህርት የሚሰጥ ከሆነ እሰየው ካልሆነ ግን ቢያንስ በዚህ አስተያየት ጥቁምታ መነሻነት መጽሀፉን አንብባችሁ የፈጠረባችሁን ስሜት በጽሁፍ ብታካፍሉን መልካም ነው ለማለት እፈልጋለሁ፡፡

***የመጽሀፉ ወቅታዊነት፣ አቀራረብና ይዘት***

በእኔ እምነት ይኸ መጽሀፍ ተዘጋጅቶ መታተም የነበረበት ከአስር አመት በፊት ኢህዴን 25ኛ አመት የልደት በአሉን ባከበረበት ወቅት ነበር፣ እንዲሁም የድርጅቱ ታሪክ በሁለት ቅጾች ተከፍሎ እንዲጻፍ ቢደረግ ኖሮ ይበልጥ ስሜት ሰጭ፣ ገላጭና የተሟላ ይሆን ነበር የሚል ግምትም አለኝ፡፡ ይህም ማለት የመጀመሪያው ቅጽ በዋነኛነት የኢህዴን የትጥቅ ትግል ታሪክ ላይ በማተኮር ማለትም ከህዳር 11/1973 ዓ.ም ዋዜማ ጀምሮ እስከ ጥር 17/1986 ዓ.ም ድረስ በነበሩት አስራ ሶስት አመታት ውስጥ የነበረውን ሁለንተናዊ የትግል እንቅስቃሴ በተለይም ድርጅቱ በትጥቅ ትግሉ ሒደት ያሳካቸውን ፖለቲካዊና ወታደራዊ ድሎች፣ የገጠሙትን ፈተናዎችና የደርግ-ኢሰፓ መንግስት ከስልጣን ከተወገደ በኋላ በሰላምና መረጋጋት ስራ ውስጥ በሀገር አቀፍም ሆነ በክልል ደረጃ የነበረውን ሚና በሚገባ በሚያሳይ መልኩ በዝርዝር እንዲጻፍ ተደርጎ መውጣት ነበረበት፡፡

ሁለተኛው ቅጽ ደግሞ ከጥር 17/1986 ዓ.ም እስከ አሁን ድረስ ያለውን ሁኔታ በሚገባ በሚያንጸባርቅ አኳኋን ማለትም በፌዴራል መንግስት ደረጃ የነበረውን ተሳትፎና የክልሉን መንግስት በአዲስ መልክ ከመመስረት ጀምሮ ከተመሰረተም በኋላ የእለት ከእለት ፖለቲካዊና መንግስታዊ እንቅስቃሴዎችን እንዴት እየመራ እንደመጣ፣ እንዲሁም የአማራን ዴሞክራሲያዊ ብሔረተኝነት ለማሳደግ የሰራቸውን ፖቲካዊና ዴፕሎማሲያዊ ስራዎች በአግባቡ በሚያሳይ መልኩ ተዘጋጅቶ ቢታተም ኖሮ ይበልጥ ስሜት ይሰጥ የነበረ ከመሆኑም በላይ በይዘትም ጥልቀት ይኖረው እንደ ነበር ከወዲሁ ለመገመት አይከብድም፡፡

ይህም ባለመሆኑ ምክንያት ይህ ሰነድ የአንድን ትልቅ ድርጅት ያውም በከፊልም ቢሆን የኢትዮጵያን ብሔር-ብሔረሰብ ህዝቦች አጠቃላይ የትግል ታሪክ የሚመለከት ጉዳይን እንደ ቀላል ነገር ጠቅለል ባለ መልኩ ለመዳሰስ የሞከረ ያልተሟላ የመረጃ መጽሄት በሚመስል መልኩ ተዘጋጅቶ በመቅረቡ ለታሪክ ተመራማሪዎችም ሆነ ለመጭው ትውልድ በማጣቀሻነት ሊያገለግል የሚችል ሰነድ ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡ ከዛም አልፎ የሀገራችን ብሔር-ብሔረሰብ ህዝቦች በአጠቃላይና በቅርብ ጊዜ ውስጥ ድርጅቱን የተቀላቀሉ አባላቱ ቀርተው የድርርቱ መስራቾችን ጨምሮ በትግሉ የመጀመሪያ ወራትና አመታት በረሀ የገቡ ታጋዮችን ትውስታ እንኳ በአግባቡ በያዘ መልኩ አደራጅቶ በመቅረብ የተሟላ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ሊያደርግ የሚችል ሰነድ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ ቀጥለው በሚቀርቡት አንቀጾች በምሳሌ አስደግፌ በዝርዝር ለመዳሰስ እንደምሞክረው ሁሉ በቂ ዝግጅት ተደርጎበትና በድርጅቱ ማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤትም ሆነ በሰማዕታት ሀውልት ውስጥ የሚገኙት የድርጅቱ የቆዩ ሰነዶች እንኳ በአግባቡ ተፈትሸው በማጣቀሻነት እንዲያገለግሉ አለመደረጉ በራሱ እንደ ትልቅ ክፍተት መታየት አለበት ብየ አምናለሁ፡፡

ከዛም አልፎ የመስራች አባላቱ ስምና ማንነት በተሟላ መልኩ ተገልጾ ከተቻለ በፎቶ ግራፍም ጭምር እንዲደገፍ ተደርጎ እንዲወጣ ያልተደረገበት ሁኔታ ሲታይ በእርግጥም የሰነድ ዝግጅቱ ያን ያህል ታስቦበት የተከናወነ ስራ ስለመሆኑ ያጠራጥራል፡፡ በዚህ ረገድ ቢያንስ የኢህዴን መስራች ከሆነው ታጋይ ህላዌ ዮሴፍ ታሪክና ጥበብ የግጥም መድብል ዝግጅት አንዳች ትምህርትና መልካም ልምድ መውሰድ ይቻል እንደነበር ሲታሰብ ደግሞ በእርግጥም በይድረስ ይድረስ ስሜት የተዘጋጀ ነው የሚለውን ሀሳብ ያጠናክራልና በጅጉ ያማል፡፡

እንዲሁም ቀደም ሲል በእህአፓ የኋላ ኋላ ደግሞ ከድርጅቱ ምስረታ ዋዜማ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በአመራርነት ያገለገሉ ሰዎች ሀሳባቸውንና ትውስታቸውን እንዲገልጹና ታሪኩ ሙሉዕ እንዲሆን በማድረግ ረገድ አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ያልተጋበዙበት ይልቁንም የመስራች አባላቱም ሆነ ከድርጅቱ ምስረታ ማግስት ጀምሮ በነበሩት ወራት ውስጥ ወደ ድርጅቱ የተቀላቀሉ ታጋዮች ማንነትና በትጥቅ ትግሉ ወቅት የነበራቸው ጉልህ አስተዋጽኦ በዝርዝር ያልቀረበበት ሰነድ በመሆኑ ያለ ማጋነን ጉድለቱ እጅግ የበዛ ሆኖ ስለምናገኘው ግን ለምን ይሆን እንዲህ እንዲሆን የተደረገው የሚል ጥያቄ እንድናነሳ ያደርገናል፡፡

ሌላው ቀርቶ ከምስረታው ጀምሮ በተካሄዱት ደርጅታዊ ጉባኤዎች የድርጅቱ ሊቃነ መናብርት (ዋና ጽሀፊዎች) ሆነው በመመረጥ ያገለገሉ ታጋዮች ስምና አጠቃላይ ስብዕና እንዲሁም በአመራር ቆይታቸው ወቅት የነበራቸው ወታደራዊና ፖለቲካዊ ሚና በትክክል ያልተገለጸበት ሰነድ ስለሆነ በእርግጥም ለማጣቀሻነት የሚበቃ የታሪክ መጽሀፍ ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡ ይህን አስተያየት በድፍረት እንዳቀርብ ያደረገኝ ዋናው ምክንያት ከላይ በአጭሩ ለመግለጽ እንደሞከርሁት የዚህ ድርጅት የትግል ታሪክ በከፊልም ቢሆን የሀገራችን ብሔር-ብሔረሰብ ህዝቦች የትግልና የድል ታሪክ አካል ስለሆነ በደንብ ታስቦበትና ጊዜ ተሰጥቶት በባለሞያዎችም ታግዞ ጭምር ጥልቀት ያለው ጥናትና ምርምር ተካሂዶ መጻፍ ሲገባው እንዲህ እንደ ዋዛ ተጠቅልሎ መቅረብ አልነበረበትም የሚል እምነት ስላለኝ ነው፡፡

ከዛም ባሻገር የኢህዴን-ብአዴን ታሪክ ወጥ በሆነ መልኩ እንዲዘጋጅ የድርጅቱ ከፍተኛ አመራር ከወሰነ በርካታ አመታትን እንዳስቆጠረ ቢነገርም ይህን ያልተሟላና ተፈላጊ ማጣቀሻዎችን እንኳ በበቂ ሁኔታና በአግባቡ ሳይዳስስ የተዘጋጀን ሰነድ አሳትሞ ለተደራሲያን ለማቅረብ በርካታ አመታትን መውሰዱ ብቻ ሳይሆን አሁን ላይ ተዘጋጅቶ የወጣው መጽሀፍ በራሱ መሰረታዊውን ነገር ሳያሟላ መቅረቡም በእጅጉ የሚያስገርም ነገር ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡ ለምን ቢባል እንደዚህ አይነት የታሪክ ሰነድ ተዘጋጅቶ ከመታተሙ በፊት ሊይዝ የሚገባውን መረጃና ማስረጃ በተቻለ መጠን አሟልቶ እንዲቀርብ ለማድረግ የተደረገው ጥረት ሲታይም እዚህ ግባ የሚባል ሆኖ አለመገኘቱ በእርግጥም ያስተዛዝባልና ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ሰነዱ ከድርጅቱ የትግል ታሪክ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ዋቢ መጽሀፍትና ጽሁፎች እንዲሁም የድርጅቱን ልዩ ልዩ ሰነዶች ጭምር በሚገባ ፈትሾ ድርጅቱ ያለፈባቸውን የትጥቅ ትግል ሒደቶች በጥልቀት ሊያሳይ በሚችል መልኩ አለመዘጋጀቱ፣ ከዛም አለፍ ብሎ የቀድሞውን ጠቅላይ ሚኒስትር ጨምሮ የህወሀት ከፍተኛ አመራሮች ከድርጅቱ ምስረታ ዋዜማ ጀምሮ በተለያየ ጊዜ ስለድርጅቱ ጥንካሬ እና መስራች አባላቱ የትግል ጽናት አስመልክተው የሰጧቸውን የምስክርነት ሀሳቦች በአግባቡ እንዲካተቱ አለመደረጉ በራሱ ሰነዱ በይዘቱ የሳሳና መያዝ የነበትን ጠቃሚ ሀሳብ ያልያዘ እንዲሆን በማድረግ ረገድ የራሱን አስተዋጽኦ አድርጓል ማለት ይቻላል፡፡

እዚህ ላይ የተወሰኑ ምሳሌዎችን በማንሳት በአዘጋጆቹ ግዴለሽነትና ስንፍና እንዲሁም በድርጅቱ ማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት ደካማ ክትትል ምክንያት ምን ያህል ጠቃሚ ሀሳቦችና ማስረጃዎች በሰነዱ ውስጥ ሳይካተቱ እንደቀሩ ለማሳየት ልሞክር፣ የኦህዴዱን መስራቾች የአቶ አባዱላ ገመዳንና የአምባሳደር ኩማ ደመቅሳን እንዲሁም የደኢህዴኑን መስራች ዶ/ር ካሱ ኢላላን የምስክርነት ቃል ተገቢ ሚዛን ለመስጠት ብንቸገር እንኳ የህወሀቶቹን ነባር ታጋዮችና ጉምቱ የፖለቲካና ወታደራዊ ባለስልጣናት ምስክርነት እንዲሁ እንደ ዋዛ ወደ ጎን ሊተው የሚገባ ጉዳይ አልነበረም የሚል ጽኑ እምነት አለኝ፡፡

ይህም ማለት እነዚህ የህወሀት ከፍተኛ አመራሮች ኢህዴንንና መስራች አባላቱን ከምስረታው ጀምሮ በሚገባ የሚያውቋቸው ብቻ ሳይሆኑ እቅፍ ድግፍ አድርገው ለድል ያበቋቸው በመሆናቸው የሚሰጡት የምስክርነት ሀሳብ ለመጽሀፉ ሙሉዕነት እጅግ ጠቃሚ ስለሆነ አዘጋጆቹ ቢዘነጉትም ወይም ሆን ብለው ቢተውትም እኔ ግን የኢህዴን-ብዘዴንን ለቲካዊና ወታደራዊ ሚና አጉልቶ በማሳየት ረገድ ትልቅ ዋጋ አለው ብየ ስለማምን የሰጡትን ምስክርነት በቅድም ተከተል ጠቅለል አድርጌ ለማቅረብ ሞክሬያለሁ፡፡

እስቲ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትርና ለረዥም ጊዜ ያህል የህወሀት-ኢህአዴግ ሊቀመንበር በመሆን እስከ ህልፈተ ህይወታቸው ድረስ ያገለገሉት አቶ መለስ ዜናዊ በ2003 ዓ.ም የኢህዴን-ብአዴን 30ኛ አመት በአል አከባበርን ምክንያት በማድረግ ከታሜሶል ኮሚኒኬሽን ጋዜጠኛ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ስለኢህዴን-ብአዴን አመሰራረትና በምስረታው ወቅት የነበረውን ነባራዊ፣ ህሊናዊና ታሪካዊ ሁኔታ ከገለጹበት የምስክርነት ቃል እንጀምር፡፡

እንደ አቶ መለስ ዜናዊ ገለጻ ከሆነ ኢህዴን የተመሰረተበት ወቅት የደርግ መንግስት አንጻራዊ የበላይነት የያዘበት ጊዜ ነበር፣ በዚህ ጊዜ አንድ አዲስ አጋር ድርጅት ተፈጠረ ማለት ለህወሀት ትልቅ ደስታንና ሞራልን የሚያስገኝ ነበር፡፡ ምክንያቱም በዚህ ወቅት ህወሀት ብቻውን የኢትዮጵያን ህዝብ አንድነት ማምጣት የሚያስችል ቁመና አልያዘም ነበር፣ አዲሲቷን ኢትዮጵያ በጽኑ መሰረት ላይ ለመገንባት ደግሞ የኢህዴን መመስረት ትልቅ ፋይዳ ነበረው፡፡ እንዲሁም አቶ መለስ ስለኢህዴን-ብአዴን መስራቾች የትግል ጽናትና ከህዝባዊ ወያነ ሀርነት ትግራይ ታጋዮችም እንዴት እንደሚለዩ ጭምር ሲገልጹ ደግሞ፡-

> *አንድ ሰው ለአንድ መስመር ወይም ለአንድ ድርጅት ህይወቱን ከገበረ በኋላ ያ ድርጅት ጭራቅ ሆኖ ያንን ግለሰብ ሊውጥ ወይም የዛን ግለሰብ ተስፋ ሊያጨልም የሚችልበት ሁኔታ ሲፈጠር የሚኖረው ሁኔታ ከሞት ያለፈ ነው፣ ከሞትም የባሰ ነው፡፡ የታገሉለት ድርጅት ጭራቅ ሆኖ አላማቸውን ሲውጥ፣ ጉም ሆኖ ሲበን፣ ሲተን እና መሀል ሜዳ ተበትነው ሲቀሩ ያ በጣም አስከፊ ሁኔታ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ለመታገል መወሰን ለህወሀት አዲስ ነው፣ ከሽዎች ወደ አስሮች ተመልሶ በጽናት መቀጠል መቻል በእርግጥም ትልቅ የሆነ የአላማ ጽናትን ይጠይቃል፣ ኢህዴኖች ያን አስከፊ ሁኔታ ተሻግረው ነው የሄዱት፡፡ ህወሀቶች እንደዚህ አይነት መጥፎ ዕድል አልገጠመንም፡፡*[1]

በማለት ነበር በወቅቱ ኢህዴን ውስጥ የነበረውን ፈታኝ ሁኔታ በሰላ አንደበታቸው ያረጋገጡትና የኢህዴን-ብአዴን መስራች ታጋዮችም ሆኑ የተከታዮቻቸው የጽናት ደረጃ ምን ያህል ከብረት የጠነከረ እንደነበር የገለጹት፡፡ በአጠቃላይም አቶ መለስ

---

[1]ይኸንን ግልጽ የሆነ የምስክርነት ቃላቸውን አደምጦ ለሚረጋገጥ የሚፈልግ ሰው ዩ ቱብ ወስጥ ገብቶ መመልከት ይችላል፡፡

“ኢህዴን-ብአዴን የአማራ ክልል ህዝቦችን አታግሎ አስቸጋሪውን የደርግ ዘመን በድል አድራጊነት ማለፉ፣ ኋላም ላይ የሽግግሩን ወቅት ፈተና በጽናት መዝለቁና የ1993 ዓ.ምቱን የህወሀት አመራር ለሁለት መሰንጠቅ ተከትሎ በሀገሪቱ ላይ ሊደርስ ይችል የነበረውን ከፍተኛ የሆነ አደጋ በግንባር ቀደምነት ተንቀሳቅሶ በመቀልበስ ረገድ የተጫወተውን ወሳኝ ሚና ስመለከት ለወደፊቱም ብሩህ ተስፋን የፈነጠቀ ድርጅት ነው ብየ እንዳምን አድርጎኛል፡፡”

ሲሉ ነበር ሀሳባቸውን አጠናክረው የገለጹት፣ እንዲሁም የህወሀት ነባር ታጋይና ለረዥም አመታትም በከፍተኛ አመራርነት ማገልገላቸው የሚነገርላቸው፣ ሆኖም በ1993 ዓ.ም የህወሀትን ከሁለት መሰንጠቅ ተከትሎ በአንጃነት ተፈርጀው ከድርጅቱ እስከተሰናበቱበት 1993 ዓ.ም ድረስ የትግራይ ክልል ርዕስ መስተዳድር በመሆን ረዘም ላለ ጊዜ ያገለገሉት አቶ ገብሩ አስራት ሉኣላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ በሚል ርዕስ ጽፈው ባሳተሙት ዳጎስ ያለ መጽሀፋቸው ውስጥ ስለ ኢህዴን-ብአዴን የትግል አስተዋጽኦ አንስተው ያሰፈሩትን ሀሳብ ደግሞ ቀጥለን ለመመልከት እንሞክር፡

> የአሁኑ ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) የበረሓ ስሙ የኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኢህዴን) ነበር፡፡ ድርጅቱ ከኢህአፓ/ሠ ተገንጥለው በቀሩ ጥቂት አባላት የተመሰረተ ሲሆን በጸረ-ደርግ የትጥቅ ትግል የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ሆኖም ኢህዴን/ብአዴን ደርግን በመጣል (ረገድ) ካደረገው ወታደራዊ አስተዋጽኦ ይልቅ የፖለቲካ አስተዋጸኦው ይልቃል፡፡ (ምክንያቱም) ተህህት ኢህአሠን (በሀይል ቀጥቅጦ) ከትግራይ ካስወጣ በኋላና ኢህአፓም በይበልጥ በራሱ ውስጣዊ ችግሮች (ተተብትቦ) ከተበታተነ በኋላ ህወሀት መኻል አገር ውስጥ ከማን ጋራ ሆኖ ትግሉን እንደሚገፋ ችግሮት ነበር፡፡[2]

በማለት ነበር የኢህዴን-ብአዴንን ወሳኝ ፖለቲካዊ አስተዋጽኦ በማያሻማ ሁኔታ ያረጋገጡት፣ ከዚህም በተጨማሪ ኢህዴን-ብአዴን 35ኛ አመት የልደት በአሉን ሲያከብር በአሁኑ ወቅት የመከላከያ ኢታማዦር ሹም ሆነው የሚሰሩትና የህወሀት ነባር ታጋይ እንደሆኑ የሚታወቁት ጀነራል ሳሞራ የኑስ በሰጡት የምስክርነት ቃል በግልጽ ለማስገንዘብ እንደሞከሩት “ራያ-ቆቦ አካባቢ በተካሄደው ውጊያ ላይ ከእኔ ጋር የኢህዴን አካል የሆነችው ላብ አደር ክፍለ ጦር ተሳትፋ አባላቷ ግዳጃቸውን በሚገባ ተወጥዋል፡፡ በዚህ ወቅት ኡስማን አሸኔ[3] የተባለው የኢህዴን ከፍተኛ አመራር ነበር ከእኔ ጋር አጠቃላይ ግንባሩን እንዲመራ ተመድቦ የነበረው፡፡” በማለት ነው የኢህዴን ታጋዮች በትጥቅ ትግሉ ወቅት የደርግን ሰራዊት በመዋጋት ብቻ ሳይሆን በከፍተኛ አዋጊነትም ጭምር የነበራቸውን የነቃ ተሳትፎ ያረጋገጡት፡፡

ከዛም አልፎ የትግሉን አስቸጋሪነት፣ ድል የማድረጉን ሁኔታ አይቀሬነት፣ የአባላቱን ጽናትና አይበገሬነት ፍንትው አድርገው በማሳየት አርሶ አደሩንም ሆነ ወጣቱን ትውልድ ለትግል በማነሳሳት ረገድ ጉልህ ሚና የነበራቸው የግጥም ስንኞች በሀሳብ ማጠናከሪያነት እንደ አግባብነታቸው በሰነዱ ውስጥ እንዲካተቱ አለመደረጉ በራሱ መሰረታዊ ስህተት ከመሆኑም በላይ ተደራሲያን የትግሉን አስከፊ ገጽታ ብቻ ሳይሆን የወደፊቱን ብሩህ ተስፋ በአግባቡ መተንበያቸውን ጭምር እንዳንገነዘብ ያደረገ ይመስለኛል፡፡

ሌላው ቀርቶ አሁንም ድረስ ኢህዴንን የህወሀት ፍጡርና የድርጅቱ መስራች አባላቱንም የህወሀት አመራር ተላላኪ ሆነው የሚያገለግሉ አማርኛ ተናጋሪ ህወሀቶች እንደሆኑ ተደርገው እንዲታዩ በርካታ ሰዎች በንግግርም ሆነ በመጽሀፍ መልክ እንዲሁም የመገናኛ ብዙሀኑን ጨምሮ በተለያዩ መጣጥፎች ጥረት ማድረጋቸው ግምት ውስጥ ገብቶ እነዚህን የተዛቡ አመለካከቶችን ለማስተካከል እንዲቻል ይህን አጋጣሚ ተጠቅሞ በማጋለጥና ስህተታቸውንም በማስረጃ አስደግፎ በማረም የኢትዮጵያ ህዝብ በአጠቃላይና የአማራ ክልል ህዝቦች ደግሞ በተለይ እንዲሁም በቅርቡ ድርጅቱን የተቀላቀሉ አባላት የመሪ ድርጅታቸውን ትክክለኛ ታሪክ በአግባቡ እንዲያውቁ ጥረት አለመደረጉ ታሪካዊ ስህተት እንደሆነ ይሰማኛል፡፡

በተለይም በቅርቡ ታትመው ከወጡትና የበርካታ ኢትዮጵያዊያንን ቀልብ በእጅጉ ስበው ከነበሩት መጽሀፍት መካከል የአቶ ገብሩ አስራትና የኮሎኔል ፍስሀ ደስታ ስራዎች ስለ ኢህዴን አመሰራረትና ፖለቲካዊ ሚና ያሰፈሩትን ሀሳብ በጥልቀት ተመልክቶ በማስተባበልም ሆነ ሁኔታውን በማስረጃ አስደግፎ ይበልጥ በማብራራት ረገድ በዚህ የታሪክ ሰነድ ውስጥ ምንም ነገር አለመባሉ እውነት ነው የምላችሁ በጣም የሚያሳዝን ድርጊት ነው፡፡

---

[2]ገብሩ አስራት (2007)፣ ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ፣ 4ኛ እትም፣ ገጽ 108፣

[3]ኡስማን አሸኔ ከኢህዴን መስራቾች ወስጥ አንዱ የነበረ ከመሆኑም በላይ በጊዜው የኢህዴን/ኢህአዴግ ከፍተኛ አመራር በመሆን የሚታወቅ ሲሆን በ1982 ዓ.ም ወልዲያ ከተማ ከተያዘ በኋላ ህይወቱ አልፏል፡፡

ከዚህም ባሻገር የመስራች አባላቱን ዝርዝር የሚያሳየውን ሰንጠረዥ ጨምሮ በተደጋጋሚ በዋቢነት የተጠቀሱ አመራሮችና መስራች አባላት ስም ከእነ አባታቸው ብሎም የትግል ስማቸው በተገቢው መጠቀስ ሲገባው የብዙዎቹ ነጠላ ስማቸው ብቻ መቀመጡ አንድም ስመ ሞክሼ ሰው ቢኖር አንዱን ከሌላኛው ለመለየት የማያስችል እንዲሆን አድርጓል፣ ሁለትም በትጥቅ ትግሉ ወቅት ለየት ባለ ስያሜ የሚታወቁ የድርጅቱ አመራሮችንና ተታጋዮችን በግርጌ ማስታወሻ ወይም በቅንፍ ውስጥ አንኳ አስቀምጦ ተደራሲያን በአጠቃላይና የአህዴን ታጋዮችና የነባር ነጻ መሬት ነዋሪዎች በተለይ የተሻለ ትውስታ እንዲኖራቸው ማድረግ አለመቻሉ እንደ አንድ ትልቅ ክፍተት ተደርጎ መታየት ያለበት እላለሁ፡፡ በዚህ ረገድ፡-

አዲሱ ለገሰ (አዲሱ አቦ) ለምን ተባለ?

ተፈራ ዋልዋ፣ የሚለው ስም እንዴት ሊወጣለት ቻለ?

ታደሰ ካሳ (ጥንቅሹ) የተባለበት ምክንያት ምን ይሆን?

ተሾመ እሸቱ (ሀባር) የሚል ስያሜ ለምን ተሰጠው?

ዮሴፍ ረታ (ገይድ) የመባሉ ምክንያት ምን ይሆን?

አባተ መኮንን (ጎንቢሶ)፣ ለምን እንደተባለ?

ይርጋ አበበ (ሀው ጃኖ)፣ ለምን አልተጠቀሰም?

ከበደ ጫኔ (ጣሳ) የተባለበት አጋጣሚ ምን ይሆን?

የሚሉት በግንባር ቀደምነት ሊጠቀሱ የሚችሉ መስራችና ነባር ታጋዮች ይመስሉኛል፣ ጸሀፊዎቹ በትግሉ ሒደት ውስጥ የነበሩ የተለያዩ ክስተቶችን እና እነዚህን ክስተቶች ተከትሎ በድርጅቱ እንቅስቃሴ ላይ ይፈጥሩት የነበረው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ሁኔታ በአግባቡና በዝርዝር ተዘግቦ እንዳይገኝ የሚያደርግ አቀራረብን በመከተላቸው ምክንያት በርካታ ሁኔታዎች ሳይካተቱ እንዲቀሩ አድርጓቸዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጽሁፍ መግቢያ ላይ አጽንኦት ሰጥቼ ለመግለጽ እንደሞከርሁት የኢህአፓ ዋነኛ ክፍል ከነበረው የበለሳው ዴመክራሲያዊ የእርማት ንቅናቄን መነሻ በማድረግ  የተመሰረተ የፖለቲካ ድርጅት እንደ መሆኑ መጠን የክፍሉ ታደሰን ያ ትውልድ መጽሀፍትን፣ የአምባሳደር ህላዌ ዮሴፍ ታሪክና ጥበብ እና ሌሎች በኢህአፓ ታሪክ ዙሪያ የተጻፉ ልዩ ልዩ ሰነዶችን በዋቢነት ሳያካትት የወጣ ሰነድ መሆኑና ይህ ሁኔታ የተፈጸመው ደግሞ አብዛኛዎቹ መስራች አባላት በህይወት እያሉ መሆኑ ሲታሰብ በእውነት በእጅጉ ያስቆጫል፡፡

ከዛም አልፎ ከምስረታው በፊት ለበርካታ ወራት (ከአምስት ወር ላላነሰ ጊዜ) በእርማትና በመስመር ማጥራት እንቅስቃሴ ውስጥ ላለፈና ይህንንም የእርማትና የመስመር ማጥራት ስራ በበርካታ ጥናታዊ ጽሁፎች አስደግፎ ለመስራች አባላቱ ለማብራራት ጥረት ላደረገ ንቅናቄ በርካታ ቃለ ጉባኤዎችና የማብራሪያ ጽሁፎች ተጠቅሰው ሰነዱ በእጅጉ የሚዳብርበት ሁኔታ አለመፈጠሩ ሲታይ እነዚህ ሰዎች ከታሪክ አጻጻፈፍ ስልትም ሆነ በተለያዩ ግለሰቦች ከተጻፉ መጽሀፍት ያን ያህል የራቁ ናቸው እንዴ የሚል ጥያቄ እንዳነሳ አድርጎኛል፡፡

እንዲሁም በንቅናቄው ውስጥ ከፍተኛ ሚና የነበራቸው አመራሮችና ግንባር ቀደም የትግሉ ተዋናዮች የግል ማስታወሻ በበቂ ሁኔታ በማጣቀሻነት እንኳ እንዲያገለግል አለመደረጉ (የአንድ ሰው የግል ማስታወሻ ያውም አንድ ጊዜ ብቻ ከመጠቀሱ በስተቀር፣ እሱም ቢሆን ከአዘጋጆቹ አንዱ ስለሆነ ይመስለኛል)፣ የችግሩን ደረጃ በእጅጉ ያገዝፈዋል፡፡ ባለፉት 36 አመታት ውስጥ ከአስራ አንድ በላይ ድርጅታዊ ጉባኤዎችን፣ ለቁጥር የሚያታክቱ የስራ አስፈጻሚ (ፖሊት ቢሮ) እና የማዕካላዊ ኮሚቴ ስብሰባዎችን ላካሄደ የፖለቲካ ድርጅት ቃለ ጉባኤዎች ውስጥ የአንድ ድርጅታዊ ጉባኤ ቃለ ጉባኤ ብቻ መጠቀሱ ሲታይ አንድም በድርጅቱ ውስጥ የሰነድ አያያዝ ችግር መኖሩን ሊያመለክት ይችላል፣ ሁለትም ይህ ታሪካዊ ሰነድ ተዘጋጅቶ እንዲታተም ይሁንታ የሰጠው አመራርም ሆነ በዝግጁ ላይ በቀጥታ የተሳተፉት ሰዎች ለድርጅቱ ሰነዶች ያን ያህል ዋጋ አለመስጠታቸውን በግልጽ ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ከ39 ያላነሱ መስራች አባላትን ይዞ የተደራጀና በሒደቱም ከፍተኛ

የሆነ የፖለቲካ ክረክር እያካሄደ አልፎ አልፎም ቢሆን የልዩነት ሀሳቦችን እያስተናገደ የመጣን ድርጅት ታሪክ ሲጻፍ የአንድ አባል ማስታወሻ ብቻ ተጠቅሶ መታለፉ ተገቢ አይደለም፡፡

እንዲሁም በትጥቅ ትግሉ ወቅት የኢህዴን ሰራዊት የነበረውን ሚና በሚገባ በሚያሳይ አኳኋን የተጻፉት የብርጋዴር ጀነራል አከለ አሳየ መጽሀፍት እንኳ በዋቢነት አለመጠቀሳቸው ሲታይ ደግሞ ጸሀፊዎቹ የግላቸውን ትውስታ ብቻ መሰረት አድርገው ያዘጋጁትና ሌሎች መስራቾችም ሆኑ የድርጅቱ ነባር ታጋዮች ሀሳባቸውን እንዲያካፍሉም ሆነ የግል ማስታዎሻዎቻቸው በማጣቀሻነት እንዲያገለግሉ ያልተደረገበት ሰነድ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

የሚገርመውና በእጅጉ የሚያሳዝነው ነገር ደግሞ ሰነዱን በሀላፊነት እንዲያዘጋጁ በማዕከላዊ ኮሚቴው የተመረጡት የድርጅቱ መስራችና አመራር አባላት ድርጅቱን ለረዥም ጊዜ ያህል በስራ አስፈጻሚነትና በማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነት ያገለገሉ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ይህንን ሰነድ አዘጋጅታቸው ለህትመት ከማብቃታቸው ቀደም ብለው የየግላቸውን ፖለቲካዊ አቋምና የትግል ትውስታ ሊያንጸባርቁ የሚችሉ የፖለቲካና የገጥም መጽሀፍትን አዘጋጅተው በማሳተም ለተደራሲያን በማቅረብ ረገድ የተሻለ ልምድ ያላቸው ሆነው ሳለ በዚህ ሰነድ ዝግጅት ላይ የዚህ አይነት የግብር ውጣ ስራ በመስራት ግዴለሽነት የተንጸባረቀበት አቀራረብ መከተላቸው የችግሩን ስፋትና ጥልቀት ይበልጥ የሚያጎላው ይመስለኛል፡፡

የ36 አመት የትግል ታሪክ ያለው የፖለቲካ ድርጅት ቀርቶ የ36 አመት ዕድሜ ያለው ጎልማሳ ግለ ታሪክ ሲጻፍ እንኳ በተቻለ መጠን ጥንቃቄ በተሞላበት አኳኋን ተደራጅቶና የበርካታ ሰዎችን አስተያየት ታሳቢ አድርጎ ነው ለህትመት የሚበቃው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ መነሳት ያለበት መሰረታዊ ጉዳይ ደግሞ ኢህዴን-ብአዴን ባሳለፋቸው አስር የትጥቅ ትግልና ሶስት የሰላምና ማረጋጋት አመታት ውስጥ ምን ያህል ታጋዮች ተሰው የሚለው ሁኔታ ነው፣ በዚህ ረገድ ለምሳሌ ህወሀት ከስልሳ ሽህ ያላነሱ ታጋዮች መስዋዕት እንደሆኑበት በተደጋጋሚ ሪፖርት ሲያደርግ ይደመጣል፣ ኢህዴንስ ምን ያህል ታጋዮችን ሰውቶ ነው ለድል የበቃው?

እኔ ባለኝ መረጃ መሰረት እስከአሁኗ ስአት ድረስ ከኢህዴን ጋር ተቀላቅለው ሲታገሉ በነበረበት ወቅት የተሰው ታጋዮች ቁጥር በግልጽ ሲነገርም ሆነ ሪፖርት ሲደረግ አልሰማሁም፣ ለምን? ቢያንስ በዚህ ሰነድ ላይ ቁጥሩ መገለጽ ነበረበት እላለሁ፣ አሊያም አስካሁን ድረስ ሊገለጽ ያልቻለበት ምክንያት ተብራርቶ መቀመጥ የነበረበት ይመስለኛል፡፡ ሌላው በዚህ ሰነድ ውስጥ ሊነሳ የሚገባው አንድ እጅግ ጠቃሚ የሆነ ጉዳይ ደግሞ በድርጅቱ ውስጥ ሀሳብን በነጻነት የማራመድ ሁኔታን አስመልክቶ በሰነዱ ላይ የሰፈረው አገላለጽ በድርጅቱ ውስጥ ምንም አይነት ችግር እንዳልነበረ አድርጎ ከማቅረቡም በላይ ቢያንስ አልፎ አልፎም ቢሆን ይከሰት የነበረውን ጸረ-ዴሞክራሲያዊ አካሄድ በእጅጉ የሚሸፋፍን ሆኖ መገኘቱ ነው፡፡

ይህም ማለት ኢህዴን-ብአዴን ከምስረታው ጀምሮ የሀሳብ ፍጭትንና ልዩነቶችን በማቻቻል እንዲሄዱ ለማድረግ እየሞከረ የመጣ እንደሆነ ቢታወቅምና እኔም የማምንበት ቢሆንም በሰነዱ ውስጥ በተገለጸው መልኩ ሙሉ ለሙሉ ከጉድለት የጸዳ ነበር ለማለት ግን ስለድርጅቱ ካለኝ መረጃና አንጻራዊ እውቀት አንጻር ስመዝነው ያን ያህል ፍጹም ነበር ለማለት የሚያስደፍር ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ነበር ብሎ መደምደም የሚቻል አይመስለኝም፡፡ ይህንንም ሀሳቤን በማስረጃ አስደግፌ ለመግለጽ ያህል ሁለት በሚገባ የማውቃቸውን ምሳሌዎች ብቻ አንስቼ በሚከተለው መልኩ ለማቅረብ እሞክራለሁ፡

**ምሳሌ አንድ፡** በ1981 ዓ.ም በኢህዴን ውስጥ የነበረው የማርክሲስት ሌኒኒስት ሀይል ራሱን ችሎ ይደራጅና የመሪነት ሚናውን ይወጣ የሚል ሀሳብ የከፍተኛ አመራሩ አካል ከነበሩ ሰዎች መካከል ተነስቶ ውይይት በተደረገበት ወቅት የተወሰኑ የድርጅቱ መስራች አባላት የተለየ አመለካከት በመያዛቸው ምክንያት የወረደባቸው የሂስ መዓትና ይህን ተከትሎ ከድርጅቱ ይባረሩ የሚል ሀሳብ እስከማቅረብ ተደርሶ የነበረ መሆኑ ሲታይ በድርጅቱ ውስጥ ኢ-ዴሞክራሲያዊ የሆነ የትግል ስልት በግልጽ ተንጸባርቆ እንደነበረ ያመለክታል፡፡

ይባስ ብሎም እነዚህ ታጋዮች ለዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ህይወታቸውን ለመስጠት ዝግጁ ሆነውና ከምስረታው ጀምሮ ያን ሁሉ መከራና ስቃይ በጸጋ ተቀብለው እያስተናገዱ መጥተው ድርጅቱ አንጻራዊ የሆነ ጥንካሬ ማግኘት በጀመረበት በዛን ወቅት በአሁኑ ወቅት የኮምኒስት ፓርቲ ለማደራጀት የሚስችል ነባራዊም ሆነ ህሊናዊ ሁኔታ የለም፣ ለመሆኑ ማነው ኮሚንስት ታምራት ወይስ ታደሰ? ወዘተ. በማለት የመከራከሪያ ሀሳብ በማቅረባቸው ብቻ ከድርጅት እንዲባረሩ ሀሳብ ቀርቦ የነበረ መሆኑ ሲታይ የሀሳብ ነጻነት ነበር የሚለው አቀራረብ እውነታውን በትክክል ሊገልጽ እንደማይችል እንገነዘባለን፡፡

ይባስ ብሎም እነዚህ መስራች ታጋዮች የተለየ ሀሳብ በመያዛቸው ብቻ ከመባረር በመለስ ነገር ግን ከሀላፊነታቸው እንዲነሱ ተደርጎ በተራ አባልነት እንዲቀጥሉ የተወሰነበትና ከከፍተኛ አመራሩም ሆነ ከግንባር ቀደም ካድሬዎች በተለይም ከኢማሊሀ አባላት ለተወሰነ ጊዜ ያህልም ቢሆን ተገልለው እንዲቆዩ የሚያደርግ ፖለቲካዊ ሁኔታ ተፈጥሮ የነበረበት የትግል አግባብ የነበረ በመሆኑ የሰነዱ አዘጋጆች በሰፊው የደሰኮሩለትን ያህል የድርጅቱ አመራር ያን ያህል ዴሞክራሲያዊ ነበር ለማለት የሚያስችል እንዳልነበር በተለይም ለነባሮቹ የኢህዴን-ብአዴን ታጋዮች ብዙም የተሰወረ ጉዳይ አይደለም ብቻ ሳይሆን ይልቁንም ለትምህርት በሚሆን መልኩ ችግሩ ቢጠቀስና በአግባቡ ቢቀመር መልካም ነበር እላለሁ፡፡

በዚህ ረገድ ታጋይ ዮሴፍ ረታ (ገይድ) እና ታጋይ ተሰማ ገ/ህይወት ላይ የተወሰደው የቅጣት እርምጃና የማግለል ተግባር ግለሰቦቹ አይበገሬና የመርህ ሰዎች ስለነበሩ የተሰፋ መቁረጥ ስሜት ሳያሸነፋቸው በጽናት ተወጡት እንጂ በጊዜው በሞራላቸውና በመታገል ስሜታቸው ላይ ፈጥሮት የነበረውን አሉታዊ ጫና በቅርብ ለምናውቃቸው ሰዎች ግልጽ ነበር፡፡ በነገራችን ላይ ከእነዚህ አይበገሬ ታጋዮችና የመርህ ሰዎች ጋር አብሬ በመታገሌና በመስረቴም ከፍተኛ የሆነ ክብርና ኩራት ይሰማኛል፡፡ የሚገርመው ነገር የእነዚህ ሁለት መስራች አባላትና አመራሮች የአመለካከት ጥራትና የትግል ጽናት በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችል ከመሆኑም በላይ አሁንም ድረስ በንጽህና ለድርጅታቸው አላማና መስመር ቀጣይነት በጽናት የቆሙ ለቅንጦትና ድሎት ቦታ የማይሰጡ እውነተኛ ታገዮች በመሆቸው ታሪካቸው በአግባቡ ሊጻፍና ለመጭው ትውልድ ሊተላለፍ ይገባል የሚል እምነት አለኝ፡፡ ይህንንም ሀቅ በ1983 ዓ.ም አጋማሽ ላይ ሀገረሰላም ውስጥ በተካሄደው የኢህአዴግ መስራች ጉባኤ ላይ የሚሳተፉ አባላትን ለመምረጥና በጉባኤው አጀንዳዎች ላይም ለመምከር አላማጣ ከተማ ውስጥ ተዘጋጅቶ በነበረውና እኔም በተሳተፍሁበት የካድሬዎች መድረክ ላይ ታጋይ ዮሴፍ ረታ (ገይድ) በተፈጸመበት የማግለል ድርጊት ስሜቱ በእጅጉ ተጎድቶ እንደነበረ በግልጽ ማንጸባረቁ ይታወሳል፡፡

የሚገርመው ነገር እነዚህ የመርህ ሰዎችና ንጹህ ታጋዮች በወቅቱ በድፍረት ያራመዱት ፖለቲካዊ አቋምና ይዘውት የነበረው የተለየ ሀሳብ የኋላ ኋላ ትክክል እንደነበር በተግባር ተረጋግጦ ድርጅቱም ውሾን ያነሳ ውሾ በሚል አይነት አቀራረብ የኮሙኒስት ፓርቲው አባላትም በስርአቱ እንኳ እንዲያውቁትና ሀሰባቸውንም እንዲሰጡበት ሳይደረግ መቅረቱ ነው፡፡ በሌላ አባባል የኮሚኒስት ፓርቲው ህልውና ማብቃቱ በግልጽ ተነግሯቸው የቀብር ስነስርአቱን እንኳ በአግባቡ እንዲፈጽሙ ሳይደረግ በከፍተኛ አመራሩ ውሳኔ (ምናልባትም በአቶ መለስ ዜናዊና የቅርብ ሰዎች ዕውቅና ብቻ) እንዲፈርስ ተደርጎ ድርጅቱ ወደ ቀደመ ይዞታው የተመለሰበት ሁኔታ እንደነበር ይታወቃል፡፡

እነዚህ ታጋዮች በወቅቱ ባራመዱት ትክክለኛ ሀሳብና በያዙት የተለየ ፖለቲካዊ አቋም ምክንያት በአመራሩና በየደረጃው በነበሩት ካድሬዎች አማካኝነት ከአባላት እንዲገለሉ በማድረግ ለተፈጸመባቸው ግፍና በደል በይፋ ይቅርታ አለመጠየቃቸው ብሎም በዚህ ሰነድ እንኳ ይኸው ሁኔታ በግልጽ ተጠቅሶ እውቅና እንዲሰጠው አለመደረጉ ሲታይ ደግሞ አሁንም የኢህዴን-ብአዴን ከፍተኛ አመራርና የሰነዱ አዘጋጆች ከስህተታቸው ለመማርና እውነትን ፊት ለፊት ለመጋፈጥ ዝግጁ አለመሆናቸውን ሊያሳይ ካልሆነ በስተቀር ሌላ ምን ሊባል ይችላል?

ከዛም አልፎ ስለኮምኒስት ፓርቲው ምስረታ ሒደት በሰነዱ ውሰጥ በተወሰነ መልኩም ቢሆን የተባለውን ያህል ፓርቲው እንዲፈርስ የተደረገበት አካሄድ በተለይም የፓርቲው አባላት ሳይወያዩበትና እንዲያውቁት ሳይደረግ እንዲሁ በጥቂት ከፍተኛ አመራሮች መልካም ፈቃድ ላይ ተመስርቶ እንደተቋቋመ ሁሉ አሁንም በእነዚሁ ጥቂት አመራሮች ውሳኔ አማካኝነት ህልውናው እንዲቋረጥ መደረጉ ኢ-ዴሞክራሲያዊ የሆነ አከሄድን የተከተለ እንደነበር በመግለጽ ትምህርት የሚገኝበትን ሁኔታ መፍጠር ተገቢ ነበር ብየ አምናለሁ፡፡

**ምሳሌ ሁለት፡** በ1983 ዓ.ም መጨረሻ ላይ የድርጅቱ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባልና የወልዲያ ሪጅን አመራር የነበረው ይርጋ አበበ (ሀው ጃኖ) በህወሀትና በኢህዴን መካከል ያለው ግንኙነት ሚዛናዊና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አይደለም፣ ህወሀት የበላይ ኢህዴን ደግሞ የበታች ሆነው እንዲታዩ የሚደረጉ ሁኔታዎች እየተፈጠሩ መሆኑን፣ የዚህ አይነቱ ሁኔታ ደግሞ በተግባራዊ እንቅስቃሴ ውስጥም የህወሀት አባላት የበላይነት ስሜት በግልጽ እየተንጸባረቀ እንደሚገኝ አብረውት በሪጅን ኮሚቴ አባልነት ይሰሩ ከነበሩ የህወሀት አመራሮችና ተራ ታጋዮች ሳይቀር በተግባር የተመለከተውን በምሳሌ አስደግፎ ለድርጅቱ ከፍተኛ አመራር በማቅረብ ይኸ ሁኔታ በጊዜ ሊታረም ይገባዋል የሚል አቋም ማራመዱና ይህንን እምነቱንም በጽሁፍ ጭምር አዘጋጅቶ መላው የድርጅቱ አባላት እንዲወያዩበት መጠየቁ ይታወቃል (በወቅቱ አንዳንድ የህወሀት ታጋዮች ከኢህዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ይልቅ የህወሀት ተራ ታጋይ የተሻለ አቅም አለው የሚል ሀሳብ ያራምዱ ነበር)፡፡ ሆኖም ይህንን ፖለቲካዊ አቋሙን ለማስቀየር በአቶ መለስ ዜናዊና ታምራት ላይኔ ጭምር ተሞክሮ የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ

በህወሀት ሰዎች ግፊትም ይሁን የኢህዴን አመራር በራሱ ተነሳሽነት እስካሁንም ድረስ እርግጠኛ ባልሆንሁበት ሁኔታ ይርጋ አበበ (ሀው ጃኖ) የያዘው ፖለቲካዊ አቋም አደገኛና ከእህት ድርጅት ጋር ያለንን ግንኙነት የሚያሻክር ነው በሚል ሽፋን ከማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነት እንዲታገድ ተደረገ፡፡

ከዛም አልፎ አስተሳሰቡም ወደ ኢህዴን ሰራዊ አባላትና ክፍለ ህዝቦች እንዳይወርድ የታፈነበት አጋጣሚ የነበረ ከመሆኑም በላይ የኋላ ኋላ ለህይወቱ መጥፋት ምክንያት የሆነውን የይታሰር ውሳኔ አሳልፎ እሱን ለማሰር በተደረገ ግብግብ ንጉሴ ጂሞ የተባለውን የማዕከላዊ ኮሚቴ አባልን ገድሎ እሱም የተሰዋበት አጋጣሚ መፈጠሩ ሲታይ የውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲ ምን ያህል ችግር እንደነበረበት በግልጽ ያመለክታል፡፡

ይህም ሆኖ በርካቶች እውቅና ለመስጠት ይቸገሩ እንጂ ባለፉት 40 አመታት በሀገራችን በተካሄዱ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የኢህዴን-ብአዴን ወታደራዊ አስተዋጽኦ እና ፖለቲካዊ ሚና እጅግ ወሳኝና ግዙፍ የነበረ ከመሆኑ አንጻር ሲታይ የትጥቅ ትግል ታሪኩ በትክክል ተጽፏል ለማለት ባይቻልም በመነሻነት ሊታይ የሚችል ሰነድ መኖሩ በራሱ መልካም ስለሆነ በተደራሲያን ዘንድ ሊነበብና በሒደትም ሊዳብር ይገባዋል ባይ ነኝ፡፡

በሌላ አነጋገር ከዚህ ቀደም በትንንሽ ሰነዶች ላይ ሰፍሮ የነበረውንና በተወሰነ መልኩም ቢሆን አዳዲስ ሀሳቦችን ያካተተ ዳጎስ ያለ ሰነድ  እንዲኖር መደረጉ በራሱ የተሻለ ነው በሚለው አባባል አጥብቄ ስለማምን ይህንን ሰነድ እንደ አንድ መነሻ በመውሰድ የጎደለውን ለማሟላት በሚደረገው ጥረት ውስጥ ሁለገብ የሆነ ስራ ሊሰራ ይችላል የሚል እምነት ስላለኝ የድርጅቱ አባላትና ደጋፊዎች ብቻ ሳይሆኑ የዚህ ድርጅት ታሪክ በቀጥታም ሆነ በተዛዋሪ ይመለከተናል የሚሉ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ሰነዱን አግኝተው ሊያነቡትና በድርጅቱ የትግል ሒደት ላይ ያላቸውን ሀሳብም እንዲገልጹ እጋብዛለሁ፡፡